# Asylum Advice

## ከማጣሪያ ቃለ መጠይቅ በፊት

# ከማጣሪያ ቃለ መጠይቅ በፊት

## 2.1 የጥገኝነት ማመልከቻ ማጣሪያ ጥያቄ

Home Office እርስዎን በክብር፣ በማክበር እና በፍትሀዊ መልኩ ያለ እድሜ፣ የአካል ጉደት ብሔር፣ ዜግነት፣ ዘር ጾታ፣ የጾታ መገለጫ፣ ሐይማኖት ወይም እምነት ተመርኩዞ መድሎ ሳይፈጽም ያስተናግድዎታል።

በዩናይትድ ኪንግደም የቪዛና ኢሚግሬሽን (UKVI) የ Home Office አካል የሆነ መ/ቤት ነው። የጥገኝነት ማመልከቻዎን የማየት ሀላፊነት ያበት የዩናይትድ ኪንግደም (UK) መንግስት አካል ሲሆን እርስዎ በትውልድ ሀገረዎ ውስጥ በአደገኛ ሁኔታ ውስጥ መኖርዎን ወይም ያለ መኖርዎን እና በዩናይትድ ኪንግደም (UK) ውስጥ አለም አቀፍ ጥበቃ እንደሚያስፈልግዎት የመወሰን ኃላፊነት አለበት።

በጥገኝነት ማመልከቻ ሂደት በጣም ብዙ ደረጃዎች ያሉ ሲሆን ይህ የማመልከቻ ሂደት የሚወስደው ጊዜ በእርስዎ ሁኔታዎች ላይ ይመሰረታል። ግን ጉዳይዎ በመታየት ላይ እያለ ከዩናይትድ ኪንግደም (UK) እንዲወጡ አይደረግም።

በተለምዶ የመጀመሪያው ደረጃ የማጣሪያ ቃለ-መጠይቅ ሲሆን ይህም የጥገኝነት ማመልከቻዎን ለመጀመሪያ ጊዜ ሲያቀርቡ ተግባራዊ መሆን ያለበት ነው።

የማጣሪያ ቃለ-መጠይቁ ዋናው ምክንያት የእርስዎን ማንነት፣ ወደ ዩናይትድ ኪንግደም (UK) እንዴት እንደደረሱ እና ለኖርዎት የሚችሉትን ልዩ ልዩ ፍላጎቶች ለመወሰን ነው።

ዋና የቃለ መጠይቅ ክፍል (ዋና የጥገኝነት ማመልከቻ ቃለ-መጠይቅ) በኋላ ላይ የሚደረግ ይሆናል። በዋና ቃለ-መጠይቅ ጊዜያት እርስዎ እና ቤተሰብዎ በዩናይትድ ኪንግደም (UK) ውስጥ ቃለ-መጠይቁን ለምን ለማድረግ እንደፈለጋችሁ እና በዩናይትድ ኪንግደም (UK) ውስጥ ከለላ ያስፈለጋችሁ ምክንያት ለመድረስ ማብራሪያ ትሰጣላችሁ። የጥገኝነት ማመልከቻ ማጣሪያ ሂደት የእርስዎ ጥገኝነት ማመልከቻ ለመመዝገብ፣ ሁሉንም የግላዊ ዝርዝሮች ለመመዝገብ እና ስለ እርስዎ ሁኔታ {1} አጠር ያሉ {2} ዘርዘር ያሉ ሁኔታዎችን ለመጠየቅ ነው። በቃለ-መጠይቅ ሀላፊው በወንድ ወይም በሴት ቃለ-መጠይቅ አድራጊው ለመጠየቅ እንደሚመርጡ ይጠየቃሉ።

በዚህ ደረጃ ላይ ስለጥገኝነት ማመልከቻዎ በጥልቀት ምንም አይነት መረጃ አይጠየቁም፡፡

እባክዎን በዚህ ዋና የፍሬ ነገር ቃለ-መጠይቅ ደረጃ ላይ ሊጠየቁት የሚችሉት መረጃ በማጣሪያ ቃለ-መጠይቁ ደረጃ ላይ ከተናገሩት አንጻር ወጥ ስለመሆኑ ይጠየቃሉ።

ከHome Office (ሆም ኦፊስ) ጋር ስላልዎት ሁሉም ግንኙነቶች ታማኝ መሆን አለብዎት።

ለማጣሪያ ቃለ-መጠይቁ  ወደ የጥገኝነት ጉዳይ መነሻ ክፍል ከደወሉ፣ በስልክ አንዳንድ መሰረታዊ ጥያቄዎችን ይጠየቃሉ፣ ይህም ቃለ መጠይቅዎን  መቼ መካፈል እንደልብዎት ያረጋግጣል። በዚ ጊዜ እባክዎት ሒወትዎ በቀላሉ በአደጋ ውስጥ ሊገባ ይችላል ብለው የሚያምኑ

ከሆነ Home Office (ሆም ኦፊስ) ለእርስዎ ወይም ደግሞ ስለ ከስዎ ስር የሚኖር እርስዎ የሚጠብቁስ ሰው ሁኔታ አሳውቅዋቸው።

ለየጥገኝነት ጉዳይ መነሻ ክፍል የቀጠሮ  መስመር: 0208 196 4524 ከሰኞ እስከ ሐሙስ ከ 9፡ 00 ሰዓት እስከ 4፡45 እና  ዓርብ ከ 9፡00 እስከ 4፡30።ግ

## 2.2 የጥገኝነት ጥያቄ ማጣሪያ ሂደት

ለ asylum intake unit የጥገኝነት  ማመልከቻ ካቀረቡ እና ማናቸውም ጥገኞችዎ (እንደ የትዳር ጓደኛ ወይም ለአካለ መጠን ያልደረሱ ልጆች) ካለዎት እና ማናቸውም ጥገኝዎችዎ  (እንደ የትዳር ጓደኛ ወይም ለአካለ መጠን ያልደረሱ ልጆች) በእርስዎ ማመልከቻ ውስጥ ለመካተት ፈላጎት ካላቸው፣ ከእርስዎ ጋር አብረው መቅረብ አለባቸው።

እንደ ጥገኛ የማመልከት መብት አለዎ ግን በዚህ ማመልከቻ ውስጥ እንዲካተትልዎት የሚፈልጉት ማንኛውም የተናጠለ መረጃ ካለዎት የራስዎን ጥያቄ ለማቅረብም ይችላሉ።

ወደ የጥገኝነት ጉዳይ መነሻ ክፍል ሲደርሱ፣ ወደ ቃለ-መጠይቅ ክፍል እስኪጠሩ ድረስ በእንግዳ ማረፊያ ቤት መቆየት ያስልግዎታል። የማጣሪያ ሂደቱ እስከ የወሰነ ሰአታት ሊወስድ የሚችል እና ከተቻለ የሆነ ነገር ለመብላት እና ለመጠጣት ይችላሉ። የጥገኝነት ጉዳይ መነሻ ክፍል ለቤተሰቦች እንደ ለቤተሰብ ቃለ-መጠይቅ ክፍሎች ለህፃናት መጫወቻ ስፍራ፣ መሳቢያ ወይም ቴሌቭዥን መመልከቻ ስፍራ ያካተተ አቅርቦት አለን። ቢሆንም ግን ህፃናት ልጆችዎን መንከባከብ የሚችል አንዳንድ ተግባራትን ለማከናወን የሚረዳዎ ጓደኛ ያስፈልግዎታል።

የጥገኝነት ማጣሪያ ሂደት በዛ ባሉ ክፍሎች የተከፋፈለ ነው።

ይህም የሚያካትታቸው:

- የስነ-ህይወት መረጃዎን (የጣት አሻራዎችዎን እና ፎቶግራፎችዎን ማንሳት) አካቶ ይሆናል። ለስነ-ህይወት መረጃዎ ተሰብስቦ በማጣሪያ ሂደቱ ጊዜያት ከተሰጥዎት ካርድ ይጠበቃል። ይህም የማመልከቻ ምዝገባ ካርድ (Application Registration Card ARC) ተብሎ ይጠራል። ይህም ማመልከቻ እንዳቀረቡ የሚያረጋግጥ እና ለ Home Office ያቀረቡትን ማመልከቻ የሚያረጋግጥ ነው። በዩናይትድ ኪንግደም (UK) ውስጥ የመቆየት መብት ካገኙ፣ ለውጭ ሀገር ዜጎች በዩናይትድ ኪንግደም (UK) ውስጥ የመስራት እና የመኖር መብት በሚያስገኝላቸው የባዮሜትሪክ የነዋሪነት ፈቃድ ካርድ አማካኝነት በዩናይትድ ኪንግደም (UK ) ውስጥ ለመቆየት ይችላሉ። የባዮሜትሪክ የነዋሪነት ፈቃድ ካርድ የስደተኛ ሁኔታውን እና ዩናይትድ ኪንግደም (UK ) ውስጥ ያለዎትን የስደተኛ ቆይታ ሁኔታዎች የሚያረጋግጥ ነው።
- የማንነት እና የደህንነት ማረጋገጫዎችን ማካሄድ
- የመኖሪያ አቅርቦት ሊያስፈልግዎት እንደሚችል እና በዩናይትድ ኪንግደም (UK) ውስጥ የት መኖር እንዳለብዎት ለመወሰን አንዳንድ መረጃዎችን በማሰባሰብ ሂደት ድጋፍ የሚያቀርብልዎት የመረጃ አሰባሰብ ነው።
- እርስዎ የሚጠይቁትን የማጣሪያ ቃለ-መጠይቅ ማጠናቀቅ

- ስለ እርስዎ እና ቤተሰብዎ የሚቀርቡ መሰረታዊ ጥያቄዎች
- መቼ ሪፖርት ማድረግ ማድረግ እንዳለብዎ (ለበለጠ  መረጃ የሪፖርት አቀራርብ ክፍል ይመልከቱ) ማረጋገጫ ያስፈልጋል
- ወደ ዩናይትድ ኪንግደም (UK) እንዴት መጓዝ እንዳለብዎት
- ማናቸውም የህክምና ሁኔታዎች ካለዎት ወይም ከሌለዎት
- ወደ ዩናይትድ ኪንግደም (UK) ለመሰደድ ልምን እንደመረጡ አጭር ማብራሪያ ይስጡ።
- ከብሔራዊ ደህንነት ጋር በተገናኘ የሚቀርቡ ማናቸውም የወንጀል ጥፈተኝነት እና ማናቸውም አስፈላጊ ጥያቄዎች ይቀርብልዎታል።
- በዋና ቃለ-መጠይቁ ጊዜያት ወንድ ወይም ሴት ቃለ -መጠይቅ አድራጊ ቃለ-መጠይቁን እንዲያቀርብልዎ ይመርጣሉ።
- ቤት አልባ ከሆኑ ስለ ቤተሰብ ፍላጎቶችዎ ለ Home Office ማሳወቅ አለብዎት። ከማጣሪያ ቃለ-መጠይቅ ሂደት ብኃላ በዩናይትድ ኪንግደም። Home Office (ሆም ኦፊስ) ጉዳይዎ አይቶ ወደ ጊዜያዊ መኖሪያ ቤት ሊሰጦች ይቻል ወይስ አይቻልም ውሳኔ ይሰጣችዋል። ውሳኔ ራስዎ ችሎ መኖር ገንዘብ አሎት ወይስ የሎትም ታይቶ ነው። (UK) ለ Home Office የእርስዎን ወይም የጥገኞችዎን ማናቸውም የህክምና ሁኔታዎች ማሳወቅ አለብዎት እና፣
- መድሀኒት ካለቀብዎት
- የህክምና ምርመራ ወይም እርዳታ ማግኘት ከፈለጉ
- የግርፊያ ሰለባ ከሆኑ
- በህገወት የሰዎች ዝውውር እና ወይም ብዝብዛ ሰለባ ከሆኑ
- በዩናይትድ ኪንግደም (UK) ውስጥ ህፃናት ልጆችዎ ሌላ ወላጅ ካላቸው
- ማናቸውም ህፃናት ልጆች በት/ቤት ውስጥ የመጨረሻ ፈተናዎችን እየወሰዱ ከሆነ
- ነፍሰጡር ከሆኑ

የ Home Office ሰጡአቸውን መረጃዎች የሚመለከቱ እና እርስዎ ጊዜያዊ የመኖሪያ አቅርቦት የቀረበልዎትን አካባቢ ይወስናሉ። ይህ መኖሪያ ጊዜያዊ ማእከል ነው። መኖሪያው በእርሰዎ ምርጫ ላይ የሚመሰረት ቢሆንም ግን የ Home Office የእርስዎን ሁኔታ ከግምት ውስጥ ይወስዳል።

አንድ ጊዜ  ማመልከቻዎ ከተመዘገበ ውሳኔው እርስዎ በእስር ላይ መቆየት አለብዎት ወይም የለብዎትም በሚለው ላይ ይወሰዳል። ለእስር ከተዳረጉ፣ ማመልከቻዎ፣ በ fast track (DFT) process የሚወሰን ሲሆን፣ ይህም ማለት ማመልከቻዎ ፈጣን ውሳኔ ያገኛል። የመታሰር ውሳኔ ካጋጠመዎት፣ ማብራሪያ ይቀርብልዎታል። በ DFT አካል፣ ነፃ የህግ ውክልና እንዲቀርብልዎት እድል የሚሰጥዎት ሲሆን ስለ ጥገኝነት ማመልከቻዎ ሙሉ ቃለ መጠይቅ ይቀርብልዎታል።

ማመልከቻዎ ተቀባይነት ካላገኘ፣ ከዩናይትድ ኪንግደም (UK) እስከሚወጡ ድረስ በእስር የሚቆዩ ይሆናል። የይግባኝ ማመልከቻ ብቁ ከሆኑ፣ ይህም በእስር ላይ እያሉ የሚከናወን ይሆናል።

## 2.3 እውነተኛ መሆን አለብዎት

ስማመልከቻዎ የተወሰኑ ገጽታዎች ለ Home Office እንዳይናገሩ ወይም ሙሉ በሙሉ የተለየ ታሪክዎን እንዲያቀርቡ ይመከራሉ። ይህንን ማድረግዎ ለጉዳይዎ ጎጂ ከሆነ ማመልከቻዎ ተቀባይነት እንዳያገኝ እንዲያደርግ ይችላል። እውነት መናገርዎ በጣም አስፈላጊ ነው።

በማስረጃ ላይ ያልተመሰረተ ወይም ዘለፋ አዘል የጥገኝነት ጥያቄ ካቀረቡ፣ የዘገየ ወይም በተስፋ የተሞላ ጥያቄ፣ ማመልከቻዎን ውድቅ ሊያስደርግ  የሚችል እና አንድ ጊዜ የማመልከቻዎ ሂደት ከተካሄደ በኋላ ከሀገር እንዲባረሩ ይዳርጋል። በተወሰኑ ሁኔታዎች ውስጥ ይግባኝ ከዩናይትድ ኪንግደም (UK) ከለቀቁ በኋላ ብቻ የሚቀርብ ይሆናል።

የተሳሳተ መረጃ ማቅረብ ወይም ማመልከቻዎን ለመደገፍ ሀሰተኛ ሰነዶችን ማቅረብ በወንጀል የሚያስቀጣ እና እርስዎ ይህንን አድርገው ከተገኙ ለፍርድ የሚዳረጉ ይሆናል።

## 2.4 በማጣሪያ ቃለ-መጠይቅዎ ምንም መጠበቅ እንዳለብዎ

በማጣሪያ ቃለ-መጠይቅዎ ጊዜያት የ Home Office ከእርስዎ መሰረታዊ መረጃዎችን ብቻ መውሰድ አለብዎት። ፍላጎቶችዎን ከግምት ውስጥ ማስገባት አለባቸው። ማመልከቻዎን እንዴት መወሰን እንዳለባቸው እንዲሁም ይመዝናሉ። ለምሳሌ የከለላ ጉዳዮች የሌለው ተደርጎ ከሚወሰድ አንድ ሀገር ከመጡ፣ እርስዎ ለእስር እንዲሁም ማመልከቻዎ በፍጥነት እንዲወሰን ይዳርጋል።

ወደ ዩናይትድ ኪንግደም (UK) በሚያደርጉት ጉዞ ወደ ሌላ ደህንነቱ የተጠበቀ ሀገር ከገቡ እና በዛ ሀገር ላሉ የስደተኛ ቢሮዎች ከታወቁ፣ ጉዳይዎ ለ Home Office የሶስተኛ ሃገር ክፍል ሊመራ ይችላል። ይህም  ማለት የ Home Office በዛች ሀገር የሚገኙ ባለስልጣናትን የጥገኝነት ማመልከቻዎን እንዲያዩት ይጠየቃሉ። ይህም  ወደ ተባለው ሀገር ይመለሳሉ ማለት ነው። የ Home Office ከለላ ጉዳዮች ካሉበት ሀገር መሆንዎን ሊወስን እና በፍጥነት የስደተኛ ሁኔታዎችን ለማስቻል ፈጣን የጉዳይ ፍለጋ መንገድን ለመከተል ሊወስን ይችላል። የ Home Office በፍትሃዊ እና ግልጽ መልኩ የሚያስተናግድዎ ይሆናል። እንዲሁም አግባብነት ባለው ህግ ላይ ተመስርተው ብቻ ውሳኔ ይሰጣል። አስተውሉ ቃለመተይቅ ያደረገላችሁት ጽሑፍ ወረቀት ግልባጭ ያስፈልገኛል የምትሉ ከሆነ እንዲሰጣችሁ መጠየቅ መብታችሁ ነው።

## 2.5 አስተርጓሚዎች

አስተርጓሚ ካስፈለገዎ የሚቀርብልዎት ይሆናል። ቀጠሮ ካለዎት በመቀጠል አስተርጓሚ ቀድሞውኑ የሚዘጋጅልዎት ይሆናል። የመረማመጃ አገልግሎት የሚጠቀሙ ከሆነ እና በቃለ-መጠይቅ ክፍል ሲደርሱ ማጣሪያ ቀርቦልዎት ከሆነ አስተርጓሚው ሲቀርብ ለመጠበቅ ይችላሉ።

የ Home Office ለማጣሪያ ቃለ-መጠይቁ በእርስዎ ፍላጎት ላይ ተመሰርቶ አንድ ተርጓሚ አንድ አስተርጓሚ የሚመድብ ሲሆን አስተርጓሚው እርስዎ ለቃለ-መጠይቅ አድራጋዊ የሚመልሱትን ትክክለኛ መልስ መተርጎም አለበት። ከፈለጉም ወይ ሴት ወይም ደግሞ ወንድ አስተርጓም

እንዲደረግሎት ሪመርጡ ይችላሉ።

አስተርጓሚዎች እርስዎ የሚያቀርቧቸውን ማናቸውም መረጃዎች ሚስጥራዊነት የመጠበቅ ግዴታ አለባቸው።

እባክዎን የቃለመጠይቅ አድራጊው ማናቸውም ከአስተርጓሚው ጋር የተገነኙ ችግሮች እንዳለብዎት ያሳውቁ ለምሳሌ ለመረዳት ችግር ካለብዎት። ጉዳይዎ እንዴት እንደተወሰነ ወይም በጉዳዩ ውጤት ላይ ምንም አይነት ተጽእኖ አያመጣም።

## 2.6 ቅሬታውን እንዴት ማቅረብ እንዳለብዎት

በአገልግሎቶቹ ደስተኛ ካልሆኑ ወይም የሆም ኦፊስ የስራ ባልደረባ፣ አስተርጓሚዎች ማንኛውም ከሆም ኦፊስር ጋር የተገናኙ ሰዎች በማክበር እና በክብር ካልሰተናገድዎ ወይም በሙያዊ ሰነ-ምግባር ላይ ቅሬታ ካለዎት፣ ቅሬታዎን  በዛው መሰረት ማቅረብ ይችላሉ። ክስተቱ ከተከሰተ በኋላ ወዲያውኑ ቅሬታዎን ለማቅረብ ይችላሉ።  የ Home Office(ሆም ኦፊስ) ከ3 ወራት በላይ ቆይታ ያላቸውን ቅሬታዎች የ Home Office በተለምዶ አያስተናግድም።

ቅሬታውን በጽሁፍ ማቅረብ አለብዎት። ይህም በእንግሊዝኛ ወይም በዌልዝ ቋንቋ ብቻ ይሆናል። ዩናይትድ ኪንግደም (UK) ውስጥ ካሉ ይህን ከሚከተሉት ለአንዳቸው ለመላክ ይችላሉ፡-

- በኢሜል የሚቀርቡ ቅሬታዎች complaints@homeoffice.gsi.gov.uk. የ Home Office በተለምዶ በኢ-ሜይል ቅሬታዎች በፍጥነት ምላሽ ይሰጣል።
- በፖስታ የሚላክ ከሆነም፡-UKVI, Complaints Allocation Hub, 11 Floor, Lunar House, Wellesley Road, Croydon, CR9 2BY

የሚከተሉት ነገሮች መካተታቸውን ማረጋገጥ አለብዎት:

- ስምዎ እና ሙሉ የመገኛ አድራሻዎ፣
- የቅሬታዎ (ጊዜያት ቀናት እና ቦታዎች) ሙሉ ዝርዝሮች፣
- ግንኙነት ያደረገልዎት የማንኛውም Home Office የስራ ባልደረባ ወይም የስራ ተቋራጮች ስራ ባልደረባ ስሞች፣UK Visas and Immigration (ዩከ ቪዛ ኤንድ ኢሚግረሽን) ክፍል።
- ማናቸውንም ምስክሮች (ሌላም ካለ) ይዘርዝሩ፣
- የደብዳቤዎች ወይም ወረቀቶች ቅጂዎች አግባብነት አላቸው፣
- የእስርዎ የ Home Office ማጣቀሻ ቁጥሮች

ቅሬታዎ ከ Home Office የደንበኞች አገልግሎት ክፍሎች (CSUS) በአንዳቸው ይስተናገዳል።

ቅሬታዎን አጥጋቢ እና ጊዜየውን በጠቀበቀ አኳኋን የማስወገድ ሀላፊነት አለባቸው።

የHome Office ማረጋገጫ፣ ከእርስዎ ጋር ቅሬታዎን ማን እንደሚያስተናግድ አስመልክቶ

ይልክልዎታል። ብዙውን ግዜ በ 20 ቀናት ውስጥ  ሙሉ ምላሽ ይሰጥዎታል።

ቢሆንም ግን ቅሬታዎ ከባድ የስነ-ምግባር ጉድለት እንዳስከተለ ሲጠረጠር፣ ገለልተኛ ምርመራ ለማካሄድ እስከ 12 ሳምንታት ሊወስድ ይችላል። ቅሬታ ማቅረብ የጉዳዩን አወሳሰን ተጽእኖ ውስጥ አይከተውም ወይም በውጤቱ ላይ አሉታዊ ተጽእኖ አያስከትልም።

ይህንን አስመልክቶ ማንኛውም ተጨማሪ መረጃ ካስፈለገዎ እባክዎን በሚከተለው አድራሻ ያግኙን።

የጥገኝነት ምክር Asylum Advice UK (አሳይላም አድቫይስ ዩከ) ስልክ ቁጥር 0808 8000 622

## 2.7 ወደ Asylum Intake Unit መውሰድ የሚገባዎት ሰነዶች

ማመልከቻዎን ለመደገፍ በተቻለዎት ፍጥነት ሁሉንም አስፈላጊ ሰነዶች ማቅረብዎን ያረጋግጡ።

ፓስፖርት- ፓስፖርትዎ እና  ማናቸውም እርስዎ ማመልከቻ ስር የተካተቱ ጥገኞች ፓስርፖርቶች።

የጉዞ ሰነዶች-ማናቸውም ትኬቶች እና የድንበር ማለፊያ ፈቃዶች።

የፖሊስ ምዝገባ ምስክር ወረቀት/እርስዎ ወይም ቤተሰብዎ ካላቸው።

ማንኛውም ሌላ የመታወቂያ ሰነዶች እንደ መታወቂያ ካርድ፣ የልደት፣ የጋብቻ፣ የት/ቤት ምስክር ወረቀቶች፣ የአባልነት ካርዶች ወዘተ። ይህም የእርስዎን ማንነት እና ዜግነት Home Office እንዲያረጋግጥ ይረዳዋል

የህክምና ሰነዶች- Home Office ማናቸውም የህክምና ሁኔታዎቹን እና በመውሰድ ላይ ያሏቸውን መድሀኒቶች ዝርዝሮች ለማወቅ ይፈልጋል።

የመኖሪያ ማስረጃ-በዩናይትድ ኪንግደም (UK) ውስጥ ቀድሞውንም ነዋሪ ከሆኑ፣ የመኖሪያ ሁኔታውን አስመልክቶ Home Office የሰነድ ማስረጃ እንደ የኪራይ ስምምነት ወይም የቅርብ ጊዜ የመሰረተ መገልገያ ሂሳቦች ክፍያ ለምሳሌ ጋዝ፣ ኤሌክተሪክ ወዘተ የእርስዎን ሙሉ ስም እና የዩናይትድ ኪንግደም (UK) አድራሻዎን ታሪክ የሚያሳዩ ማቅረብ አለብዎት።

በሆነ ሰው ቤት ውስጥ ነዋሪ ከሆኑ እባክዎን ከቤቱ ባለቤት እርስዎ በቤት ውስጥ ለመቆየት ወይም ላለመቆት እንደሚችሉ የሚያረጋግጥ የቅርብ ጊዜ ደብዳቤ እና የቤቱን ባለቤት ሙሉ ስም እና አድራሻ የሚያሳይ የመሰረተ መገልገያ ሂሳብ ሰነድ ማስረጃ ያቅርቡ።

ጊዜያዊ መኖሪያ ካስፈለገዎት ለምን ነባሩን ማስረጃ ከዚህ በኋላ ለመጠቀም እንዳልፈለጉ አስመልክተው ማረጋገጫ ማምጣት ያስልግዎታል።በተጨማሪም ለምን የነበሮች መኖሪያ ቦታ በአሁን ሰዓት እንደሌለ እና ለም ራስዎን ችሎመኖር እንደማይችሉ መግለጫ ማቅረብ። Home Office (ሆም ኦፊስ) እዚህ አገር ውስጥ እና የመጡበት አገር ያሉት የመኖሪያ ሂኔታ ለማወቅ ምርመራ ያካሄዳል።

የ Home Office ከእርሰዎ ዋና ሰነዶችን መውሰድ እና ይገባኛልዎ እስኪካሄድ ድረስ የሚጠብቅ ይሆናል። የሰነዶችዎ ቅጂዎች ጉዳዩ እንደተፈጸመ ወዲያውኑ ይመለስልዎታል።

## 2.8 መኖሪያ እና ጥገኝነት የጠየቁት የሚመለከት ድጋፍ

በማጣሪያ ቃለ-መጠይቅ ውሰጥ መኖሪያ እና ድጋፍ እንደምያስፈልጉት ይጠየቃሉ።

የድጋፍ መስፈርትን ማሟላትዎን ወይም አለማሟላትዎን ለማረጋገጥ ሲባል ማረጋገጫዎች ይኖራሉ።

መኖሪያ እና ድጋፍ ካስፈለገዎ፡-

መኖሪያ ካስፈለገዎ ሁሉንም ንብረቶችዎን ወደ ማጣሪያ ቃለ-መጠይቁ መውሰድ አስፈላጊ ነው።

በእርግጥም የመኖሪያ ጥያቄዎ ተቀባይነት ካገኘ እና ራስዎ ችሎ መኖሪያ ቦታ ኪራይ ራርዎ ሊከፍሉ የማይችሉ መሆንዎን ከተረጋገጠ፡ ቀጥታ በጊዜያዊ የመጀመሪያ ጊዚያዊ መኖሪያ ማእከል ከማጣሪያ ቃለ-መጠይቅ በኃላ የሚመደበ ይሆናል። ይህም ብዙ ማይሎች እርቆ የሚገኘው መኖሪያ ቦታ ሊሆን ይችላል። ማናቸውንም አጣዳፊ ፍላጎቶችዎን ለሀላፊው የግድ ማሳወቅ አለብዎት። ይህ የጊዜያዊ መኖሪያ እና ለ21 ቀናት ገደማ ብቻ የሚኖሩበት ይሆናል። ቢሆንም ግን እንደ ግለሰባዊ ሁኔታዎችዎ ተመስርቶ ለረዥም ጊዜ ሊቆዩ ይችላሉ።

እርስዎን ለመደገፍ ካልቻሉ ይህንን Home Office ማረጋገጥ ይችላሉ።

Home Office በዩናይትድ ኪንግደም (UK) እና በውጭ ሀገር ስላለዎት የገንዘብ ሁኔታ ምርመራ ያካሂዳል። እራስዎን ለመደገፍ የሚያስችል የገንዘብ ምንጭ ወይም የመኖሪያ እና የምግብ አቅርቦት ሊያሟሉልዎት የሚችሉ ይሆነ ጓደኞች ወይም ዘመዶች ካለዎት Home Office (ሆም ኦፌስ) ድጋፋቸውን የሚጠብቅ ይሆናል።

Home Office (ሆም ኦፊስ) የሚከተሉትን መረጃዎች የራስዎ እና ከሶ ስር ለሚኖር ሰዎች እንዲያቀርቡ ይጠብቃል

- የባንክ መግለጫዎ የባለፈው 6 ወር የሂሳብ ዝርዝ ዚህ አገር እና ሌላ አገሮችም ስይቀር። በተጨማሪም የሆነ ገንዘብ ከየዚህ አገር ሂሳብዎ ወደ ሌላ ቦታ የተሸጋገረ ገንዘብ ካለም ያረጋግጣል።
- ማናቸውም የሀብት ዝርዝሮች፡ እነዚህ ነገሮች ተሸጠው ራስዎን እንዲችሉ ሊረዳዎች ይሚችል ከሆነ።
- ዩናይትድ ኪንደም (UK ) ውስጥ ስለሚያካሂዱት ማንኛውም ስራ መረጃ ማቅረብ አለበት፡ የ P45 (ፕ45) የሚባል ዶኩምነት ምን ያህል ጊዜ እንደሰሩ የሚያሳይ ከአሰሪዎ ስራ እናቆሙ እና መቸ እንዳቆሙ የሚያሳይ
- ማንኛውም ዋጋ ያለው ጌጣ ጌጥ
- የሆነ ገንዘብ የነበሮት ወይም ደግሞ እዚህ አገር ሲኖሩ የነበሮት ገንዘብ ይህ ገንዘብ የት

እንዳለ እና ገንዘቡ እጅዎ ጋር ካለ

• በዩናይትድ ኪንግደም (UK) ወይም በውጭ ሀገር ያልዎት ንብረት ይህ ንብረት ሊሸጥ የሚችል ከሆነ ማረጋገጫ

• ማንኛውም በእጅዎ ያለ ገንዘብ ወይም ደግሞ እዚ አገር (UK) ሲገቡ የነበሮች ገንዘብ በአሁኑ ሰዓት ይህ ገንዘብ የት እንዳለ እና ገንዘቡ እጅዎ ጋር ነው ወይቭ ማወቅ አለብን

• ከዩናይትድ ኪንግደም (UK) የሚጠየቁት ማንኛውም ጥቅማ ጥቅም፡ ማረጋገጫ ይህ እርዳታ እንደቆመ ወይም ደግሞ የሚሰጦት እርዳታ ምን ያህል እንደሆነ የሚያሳይ ዶኩመንት ማረጋገጫ ማቅረብ አለቦት።

አንዴ እዛ ለመጀመሪያ ጊዜ የሚሰጠው መኖሪያ ቤት ቦታ ከደረሳችሁ በኋዋላ የ Migrant Help (ሚግራንት ሄልፕ) ለስደተኞች የሚረዱ ሰራተኞች ገንዘብ የማይከፈለው  የሚያስፈልጋችሁ እርዳታ እኒሰትዋችሁ፡ ውልቃዊ የሆነ ምክር እና መረጃ ይሰጥዋችዋል። በተሎም ቀጠሮ ወደ UK Visas & Immigration Asylum Support Form (ASF1) (ዩከ ኢሚግረሽን አሳይለም ሳፖርት) (አ.ኤስ.ኤፍ.1) ፎርም እንዲሞልላችሁ ይሰጣችዋል። በሚሰጣችሁ ቀጠሮም ያላችሁ ዶኩመንት በምሉ ይዛችሁ መገኘት አለባችሁ።

የመጀመሪያ መኖሪያ የሆስቴል አይነት መኖሪያ እና መሰረታዊ ምግቦች እና መጸዳጃ ቤቶች ያሚላ ነው። በዚህ ጊዜ ውስጥ ምንም አይነተ የገንዘብ ድጋፍ አይኖርዎትም። በ Scotland (ስኮትላንድ) የመጀመሪያ መኖሪያ ቤት ሲሰጦት ራስዎ ምግብ አብስሎ ነው የሚበሉት ለቀን 5ብር ለቀን ለምግብ እና ለገላ መታጠብያ ይሰጦታል።

የድጋፍ ማመልከቻዎ ከተሳካ ወደ ተለየ መኖሪያ ይንቀሳቀሳሉ። ይህም በዩናይትድ ኪንግደም (UK) ማንኛውም ቦታ ሲሆን በምርጫ ላይ ሳይመሰረት የሚቀርብ ነው። Home Office እርስዎ በተመደቡበት የመኖሪያ አካባቢ ወይም አይነት ላይ ስለማናቸውም ተጽእኖዎች እንዲያውቅ ቢደረግ ጠቃሚ ነው። ማመልከቻ ቅጽዎን ሲሞሉ ይህንን ቢያደርጉ ጠቃሚ ነው ያለበለዚያ መኖሪያዎ ለእርሰዎ ፍላጎቶች ምቹ ሆኖ ላያገኙት ይችላሉ።

እባክዎን ሁሉንም ፍላጎቶች ከጥገኝነት ድጋፍ ማመልከቻ አካሄጅ ሰራተኛ ጋር የድጋፍ ማመልከቻዎን በመሙላት ይወያዩ።

የመኖሪያ አቅርቦት ሲጠብቁ ከባልጀራዎ ጋር የሚቆዩ ከሆነ፣ የገንዘብ ድጋፍ ወደ ረዥም ጊዜ ቆይታ ወደአለው መኖሪያ እስኪቀሳቁ ድረስ አይጀመርም።

መኖሪያ ካልፈለጉ
ከባልጀሮችዎ ወይም ቤተሰብዎ ጋር የሚቆዩ ከሆነ በዚያ ለመቆየት እንደሚችሉ ማረጋገጫ ያስፈልግዎታል። መኖሪያ ብቻ ሊያቀርብልዎ የሚችሉ ከሆነ ግን የገንዘብ ድጋፍ (ለመኖሪያ ብቻ) እንዲቀረብልዎ ሊያመለክቱ ይችላሉ። ሌላ ቦታ ከዘመድዎ ወይም ደግሞ ከጉዋደኞችዎ ጋር ሲኑሩ ከቆዩ እና አሁን ግን ይህ እድል የሌሎት ከሆነ እና ሌላ መኖሪያ ቦታለው ማፈላለፍ ካለቦት የምቀጥለዎ ተሌፎን ቁጥር ተጠቅመው ከ Asylum Help (አሳይለም ሄልፕ) በ 0808 8000 623 በተሎ እንዲገናኙን እና ያለ ሞነሪያ ቤት እስከሚቀሩ ድረስ መቆየት የሎቦቶም። ሌላ ቦታ ጊዝያዊ መኖሪያ ቤት ካሎት ግን፡ እኛ ጋር ማመልከቻ እያቀረቡ እያለ ያ ጊዜይዊ

መኖሪያ ቦታዎ መቶው ይለቦትም። እከዛ ድረስ Home Office (ሆም ኦፊስ) ማመልከቻው ሊያስተዳድርሎች ይችላል። አስፈላጊ የሆነ ቦታ ካከኘሎች ደግሞ ያስውቅዋችዋል።

የመኖሪያ ድጋፍ ካልፈለጉ
ጓደኞችዎ እና ቤተሰብዎ ምግብ ሊያቀርብልዎ ወይም ዝቅተኛ ገቢ ካለዎት፣ Home Office መኖሪያ ብቻ እንዲቀርብለዎ ሊያመለክቱ ይችላሉ። g

አስፈላጊ የሆነን ድጋፍ ማመልከቻ እንዲያቀርብልዎ መገናኘቱ ጠቃሚ ነው

የ Asylum Support Application UK 0808 8000 623
www.asylumhelpuk.org

ለመኖሪያ ብቻ የሚያመለክቱ ከሆነ፣ እና ከባልጀራዎ ጋር የሚቆዩ ከሆነ፣ የገንዘብ ድጋፍ ለማግኘት ብቁ መሆንዎ እስኪረጋገጥ ድረስ አይጀመርም።

ለረዥም ጊዜ በዩናይትድ ኪንግደም (UK) ከቆዩ እና በተቻለዎት ፍጥነት ጥገኝነት ካልጠየቁ፣ ከ Home Office ድጋፍ ውድቅ ሊደረጉ ይችላሉ።

ሊቆዩበት የሚችሉበት በቂ ቦታ እንደሌለዎት እና ወይም ለኑሮ የሚያስፈልግዎትን መሰረታዊ ጉዳዮች (ምግብ፣ ሙቀት) ሊያረጋግጡ የማይችሉ ከሆነ ወይም ድጋፍ መከልከልዎ የሰብአዊ መብትዎን የሚጥስ ከሆነ፣ በመቀጠል Home Office ድጋፍዎን ለመከልከል ይችላል።

## 2.9 እራሴን ለመከንከባከብ ካልቻልኩስ?

Home Office የእርስዎን ፍላጎቶች የማጣሪያ ቃለ-መጠይቁን ሲሞላ ይመዝናል።

እርስዎን እራስዎን መንከባከብ እንደማይችሉ ሊወስን ይችላል።

ይህም ባለብዎት ከባድ ህመም የአካል ጉዳት የመማር በቃት ማጣት የአእምሮ ጤና ችግሮች ወይም በእርጅና የተነሳ የሚመጣ ብቃት ማጣት የተነሳ ሊሆን ይችላል። ከእነዚህ ማናቸውም ተግባራዊ ከሆኑ፣ በመቀጠል የማህበረሰብ እንክብካቤ ምዝና እንዲሞሉ ከማጣሪያ በኃላ ለማህበራዊ አገልግሎት ሊመሩ ይችላሉ። ግልጽ እና አስቸኳይ የእንክብካቤ ፍላጎት ካለዎት፣ የአካባቢ ባለስልጣናት ድጋፉን የማቅረብ ሀላፊነት ይኖርባቸዋል። ይህም የሚያካትተው የመኖሪያ እና የገንዘብ ድጋፍ ይሆናል።

ተጨማሪ ድጋፍ ካስፈለገዎት ግን ግልጽ እና አስቸኳይ የእንክብካቤ ፍላጎት ከሌለዎት፣ ወደ ረጅም ጊዜ መቆያዎ ሲያመሩ የሚሞላ ይሆናል። ምዘናው ማንኛውንም ተጨማሪ ድጋፍ (ለምሳሌ መሳሪያ ) እንደሚያስፈልግዎ ወይም እንደማያስፈልግዎ ይወስናል።

በቤተሰብዎ ውስጥ ግልጽ የእንክብካቤ ፍላጎት (ለምሳሌ በከባድ የአካል ጉዳት ወይም ከባድ ህመም) የሚያስፈልገው ህንፃን ካለ በመቀጠል የአካባቢው ባለስልጣናት እርስዎ በጥገኝነት ህይወት ውስጥ እያሉ ተገቢውን ደረጃ Home Office (ሆም ኦፊስ) ስለ የጥገንኝነት ጉዳይዎ እስከሚታይሎይ ጊዜ፡ ያለው እንክብካቤ እንዲያቀርቡለት ሊያስፈልግ ይችላል።

ትክክለኛው ድጋፍ መቅቡን ለማረጋገጥ በህፃናት አገልግሎቶች ሊላኩ ይችላሉ።

ይህንን ለማድረግ ምክርና መመሪያ ካስፈለገዎት እባክዎን በሚከተለው አድራሻ ያግኙን፡-

Asylum Advice UK 0808 8000 622
www.asylumhelpuk.org

## 2.10 በማጣሪያ ጊዜያት የተሰጡ ሰነዶች

Application Registration Card (ARC)
የማመልከቻ ምዝገባ ካርድ (Application Registration Card -ARC) ይሰጥዎታል።
ይህ ካርድ ማመልከቻ እንዳቀረቡ የሚያረጋግጥ ጠቃሚ ሰነድ ነው። ይህ አ.ር.ክ.ኤ(ARC) ካርድ ካልተሰጣችሁ ደብዳቤ ጥገኝነት እንደጠየቃችሁ የሚያሳይ (SAL) ሳ.አ.ል ዋና ዝርዝራቸው የያዘ ማረግገጫ ይሰጣቸዋል። ይህም የግላዊ ዝርዝሮች እና ፎቶግራፍ ያካተተ ሲሆን የተጠየቀውን ይገባናል የሚያረገግጥ ይሆናል። ደብዳቤ ይህ የ SAL (ሳ.አ.ል) ካርድ ወረቀት ወደ ARC (አ.ር.ክ) ካርድ መቸ እና የት ሄዳችሁ ማስቀየር አንደምትችሉ የሚገልጥ ይላካላችዋል። ስለዚ የሚመለከት ቀጠሮ የያዘ ደብዳቤ ሳይላካላችሁ ከቀረ እባካችሁ ወደ Central Evenets Booking Unit (CEBU) (ሰንትራል አቬንትስ ቦኪንግ) (ሲ.ኢ.ቢ.ዩ) የሚባል ክፍል በ ስልክ ቁጥር 0300 123 2235 - መስመሮችሁ ከሰኞ - እስከ ዓርብ 9.30 ጥዋት እስከ 3.00 ክፍት ናቸው።

በኤአርሲ (ARC) ላይ ያሉት የግል ዝርዝሮች ማረጋገጥ ጠቃሚ ነው። ስምህ፣ የትውልድ ቀን እና የትውልድ ሀገር በትክክለኛ መልኩ መመዝገቡን ማረጋገጥ ያስፈልጋል። አንድ ጊዜ ምዝገባ ከተካሄደ ለውጥ ማድረግ አስቸጋሪ ነው።

ካርድህ ከመግለጫህ ጋር የተያያዙ ማናቸውንም ሁኔታዎች ያረጋግጣል። ኤአርሲ (ARC) በዩናይትድ ኪንግደም (UK) ስራ ለመስራት እንደተፈቀደልህ (40) በዩናይትድ ኪንግደም (UK) ጥገኝነት ከመጠየቅህ በፊት የመስራት ፈቃድ ከሌለህ፣ ማመልከቻህን ስታቀርብ የስራ ፈቃድ ትከለከላለህ።

ካርድህ የስራ ቅጥር ከማግኘት ተከልክለሀል ይላል።

ኤአርሲ የአንተን ማንነት አያረጋግጥም ግን ጥገኝነት ስትጠይቅ ሰጥተሀቸው የነበሩትን መግለጫዎች ይመዘግባል። የገንዘብ ድጋፍ ስትቀበል ኤአርሲ (ARC) ማቅረብ ያስፈልግሀል።

ለእያንዳንዱ የቤተሰብ አባልህ ኤአርሲ (ARC) ይሰጣቸዋል። ይህንን በአስተማማኝ ሁኔታ መጠበቅህ ጠቃሚ ነው። ጥገኝነት የጠየቃችሁ ወይም ደግሞ የጠየቃችሁ ጥገኝነት ያልተቀበልዋችሁ ከሆናችሁ ዕድሚያችሁ ከ 18 በላይ ክሆነ ኣና የ (ARC) አ.ር.ክ ካርዳችሁ ክጠፈባችሁ፡ ወይም ደግሞ ተሰርቀባችሁ ከሆነ እባካችሁ በአስቸክዋይ ከ Asylum Help (አሳይለም ሄልፕ) ጋር ተገናኙ፡ እነሱ ከ Home Office (ሆም ኦፊስ) ጋር እንድትገናኙ ይረዳችዋል።

መኖሪያ ፍቃድ ካላችሁ እዚህ እንግሊዝ አገር ወይም ደግሞ ከዕድሜ በታች ከሆናችዉ ከ Home Office (ሆም ኦፊስ) በቀጥታ በሚቀጥለው ቁጥር ደውላችሁ 0300 123 2235

መታወቂያ ወረቀታችሁ ጠፍቶ፡ ተሰርቆ ወይም ደግሞ ተበላሽቶባችሁ ከሆነ አሳውቅውአቸው።

ኤአርሲህን (ARC) በመጠቀም ሰፖስታ ቢሮ ሳምነታዊ ድጋፍ የምታገኝ ከሆነ፣ የጥገኝነት ድጋፍ ክፍል ማሳወቅ አለብህ። ወደ Asylum Advice UK (አሳይለም አድቫይስ ዩከ) ስትደውሉ በ 0808 8000 622 ቁጥር እባካችሁ የሚቀጥሉት ዝርዝሮች ዝግጁ አድርጉ። በማናቸውም የ Home Office ደብዳቤ የአንተን መኖሪያ እና የገንዘብ ድጋፍ አስመልክቶ ግንኙነት ስለሚያደርግልህ ቡድን ዝርዝር ለማግኘት ትችላለህ። አዲስ ኤአርሲ (ARC) ሲዘጋጅልህ የሚላክልህን የድንገተኛ አደጋ ገንዘብ ሊያዘጋጁልህ ይችላሉ። በአከባቢያችሁ የሚገኝ ቤት ጽሕፈት ሄዳችሁ የምትፈርሙበት ቦታ እዛ ሄዳችሁ Card -ARC (አርክ) ካርዱን እንድትቀበልቱ ቀጠሮ ልያዝላችሁ ይችላል። ወደ ቀጠረው ለመገናት የሚያስፈልጋችሁ የመጉዋጋዣ ክፍያ ራሳችሁ ነው የምትችሉት።

ይህንን አስመልክቶ ተጨማሪ  ምክር እና መመሪያ ካስፈለገ የጥገኝነት ማማከር አገልግሎት ዩናይትድ ኪንግደም (UK) በ0808 8000 622 ተገናኝ

አዲሱን ኤአርሲህን (ARC) አንድ ጊዜ ከተቀበልክ የሚሰጣችሁ እርዳታ በዚሂኛው Card -ARC(አርክ ካርድ) እንዲጀመርላችሁ ይደረጋል።

## 2.11 የሪፖርት አቀራረብ መስፈርቶች – IS96

በየሳምንቱ/በየወሩ ለአንድ ለተወሰነ ጊዜ የስደተኛ ቢሮ ሪፖርት እንድታደርግ ተነግሮሀል። አይኤስ96 ተብሎ የሚታወቅ ሰነድ በዩናይትድ ኪንግደም (UK) ውስጥ ጊዜያዊ የመኖሪያ ፈቃድ በማግኘት ዙሪያ የሪፖት አቀራረብ ሁኔታዎችን እና ዝርዝር ጉዳዮችን የሚገልጽ ይሰጥሀል።

ለእስር ተዳርገው ያልነበሩ አብዛኞቹ የስደተኛ ፈቃድ አመልካቾች ወደ ማእከል ወይም ፖሊስ ጣቢያ ሪፖርት እንዲያደርጉ ይጠበቅባቸዋል።

ከሪፖርት ማቅረቢያ ማእከልህ ሶስት ማይሎች ወይም ከዚያ በላይ እርቀህ የምትኖር አመልካች ከሆንክ፣ የHome Office ድጋፍን ከጉዞ ትኬቶች ጋር ለማግኘት በቁ ነህ። የመጀመሪያ የሪፖርት ዝጅትን ከ Home Office ድጋፍ እያገኘ መሆኑን ከሚያረጋግጥ ማስረጃ ጋር ማያያዝ ያስፈልግሀል። በመቀጠል ሪፖርት ለማድረግ እንድትችል ትኬቶች ይቀርቡልሀል። እነዚህም በተለምዶ ሪፖርት ማቅረቢያ ማእከል ይሰጣሉ። በአብዛኞቹ ሁኔታዎች ውስጥ ለመጀመሪያ የሪፖርት ማቅረቢያ ዝግጅት የራስህን ጉዞ እንድታዘጋጅ ያስፈልግሀል። ይህንን ለመመለስ የሚያስፈልገው ክፍያ አይከፈልህም

የአይኤስ 96 እና የኤአርሲ ካርድህን ሪፖርት (ካርዱን ከተሰጣችሁ ብቻ) በምታደርግበት እያንዳንዱ ጊዜ ማሳየት ያስፈልግሀል።

በHome Office ካልተደገፍ ልዩ ልዩ በሆኑ ሁኔታዎች ስር የጉዞ ትኬቶችን ለማግኘት ማመልከት ትችላለህ።  በሪፖርት ማቅረቢያ ዘግጅት ላይ ከስደተኛ ቢሮ ‹‹ልዩ ልዩ የጉዞ ጥያቄ›› መጠየቅ ያስፈልግሀል። ጥያቄውን በጽሁፍ ማቅረብ እና ለጉዞ የሚሆን ገንዘብ እንደሌለህ ማስረጃ ማቅረብ አለብህ

## 2.12 በቀጠሮ መሰረት አለመፈረም የሚያስከትለው ችግር

በቀጠሮው መሰረት ሁልጊዜ መፈረም አስፈላጊ ነው። መፈረም ካልቻሉ ወደ መፈረሚያው ማእከል ከቀጠሮው ቀን አስቀድመው በመደወል የፊርማው ቀን እንዲተላለፍልዎት ማሳወቅ አለቦት (ቁጥራቸውን በአይ ኤስ 96 የሚለው ወረቀት ላይ ያገኙታል)። ለምክንያትዎም ማስረጃ ማቅረብ አለቦት። ለምሳሌ መፈረም የማይችሉበት ምክንያት በሕመም ምክንያት ከሆነ የሓኪም ወረቀት ማቅረብ አለቦት።

የእርግዝናዎ የመጨረሻዎቹ ሶስት ወራት ውስጥ ከሆኑ የፊርማው ቀን ልጅ እስኪወልዱ ድረስ እንዲተላለፍልዎት ጥያቄ ማቅረብ ይችላሉ። የሚወልዱበትን ቀን የሚያሳውቀውን ሰርትፍኬት (ማት ቢ 1) ወደ መፈረሚያው ማእከል ይዘው መሄድ አለቦት። እርሱንም ከሓኪምዎ ወይም የጤና ክትትል ከሚያደርጉልዎት (ሄልዝ ቪዚተር) ሊያገኙት ይችላሉ። ይህን ካደረጉ የመፈረሚያው ማእከል; የፊርማውን ቀን ልጅ እስኪወልዱ ድረስ ሊያስተላልፉልዎት ይችላሉ። መፈረም ካልቻሉ ለመፈረሚያው ማእከል ማሳወቅ ይኖርቦታል ወይም ደግሞ ሊረዳዎት ለሚችለው ለጠበቃዎ ማሳወቅ ይኖርቦታል።

## 2.13 ለፊርማ በሚሄዱበት ወቅት ሊወስዱ የሚገባዎት ወረቀቶች

ወደ መፈረሚያው ማእከል በሚሄዱበት ወቅት አይ ኤስ 96 የሚለውን (መፈረሚያ ወረቀት) እና  አርክ (ARC) ካርድ መውሰድ አለቦት። የመፈረሚያው ማእከል እንግሊዝ ኣገር እንዲቆዩ በተሰጠዎት መመሪያ መሰረት እየፈረሙ እንዳለ አርክ (ARC) ካርድዎ ላይ ይመዘግባሉ። ሳይፈርሙ ቢቀሩ ወይም ደግሞ ካርድዎን ቢረሱ; ካርድዎ ፖስታቤት በሚሄዱበት ወቅት ወደ መፈረሚያው ማእከል ሄደው; ካርድዎ ላይ እንደፈረሙ እስኪመዘገብ ድረስ የገንዘብ እርዳታ እንዳይወስዱ ምልክት እዲሰጥ ተደርጎ ነው የተሰራው። ፖስታቤቱ ኮድ 4 የሚል ደረሰኝ ይሰጣል። ሳይፈርሙ ቢቀሩ እና ሆም ኦፊስን ባያሳውቁ የገንዘብ እርዳታዎ  ለጊዜው ሊቋረጥ ወይም ደግሞ እንደሁኔታው ሊያቆም ይችላል።  የገንዘብ እርዳታው እንዲጀምርልዎት ወደ መፈረሚያው ማእከል ሄደው; ካርድዎ ላይ እንደፈረሙ እንዲመዘገብ ማስደረግ አለቦት።

## 2.14 የህጋዊ ምክር

በተቻለ ፍጥነት የህግ አማካሪ ብታነጋግር ጠቃሚ ነው።

የህግ አማካሪው የጥገኝነት ሂደትን አስመልክቶ መረጃ በማቅረብ፣. ሰነዶችን በመተርጎም እና ለ Home Office የሚቀርጉ  ማናቸውንም ተጨማሪ ሪፖርቶች በማዘጋጀት ሊረዳህ ይችላል።

የህግ አማካሪ ከሚከተሉት ድርጅቶች በአንዳቸወ የተመዘገበ መሆን አለበት፡

- በ Law Society of England and Wales ብቁ በሆነ ጠበቃነት
- Law Society of Scotland በቁ በሆነ ጠበቃነት
- Law Society of Northern Ireland በቁ በሆነ ጠበቃነት
- የ Office of the Immigration Services Commissioner (OISC), ደረጃ 2 እና 3 ያላቸው የተመዘገቡ አማካሪዎች። ደረጃ 2-3 ማለት አማካሪው ማመልከቻህን አስመልክቶ

ምክር ለማቅረብ እና በሁሉም የስደተኛ ማመልከቻ ጉዳዮች ሊወክል ይችላል።

• የህግ አማካሪህን በምን ደረጃ እንደ ተመዘገቡ ልታማክር ትችላለህ። ከዚህ በላይ ያሉት ድርጅቶች አርማዎች ከህግ ተወካይህ በምትቀበላቸው ማናቸውም ደብዳቤዎች ላይ ይታያሉ። የህግ አማካሪ ከእነርሱ ጋር መመዝገቡን በቀጥታ ልታረግጥም ትችላለህ።

ነፃ የህግ ምክር

ጥገኝነት ፈላጊ የሆነ ማንኛውም ግለሰብ የህግ ድጋፍ መስፈርትን አስካሟላ ድረስ ነፃ የህግ አገልግሎት ለመሻት ይችላል። ሙሉ በሙሉ ማጣሪያ ከቀረበልህ በኋላ በጥገኝነት ፈላጊ ደረጃ ትመደባለህ። ለህግ ድጋፍ ብቁ ለመሆን ዝቅተኛ ገቢ እንዳለህ እና ጉዳይህ እውነተኛ የመሳካት እድል እንዳለው ማረጋገጥ ያስፈልጋል።

Legal Aid England and Wales
የ Legal Aid Agency (ለጋል ኤድ ኤጀንሲ) ህግ ድጋፍ

የህግ አማካሪ ለማግኘት፡-

የህግ ባለሙያዎች ማህበር (Law Society)
http://www.lawsociety.org.uk/find-a-solicitor/

በ Direct Gov.:
በ www.gov.uk/find-a-legal-adviser

በ OISC – Level 2 / level 3 (Specialist):
በ http://oisc.homeoffice.gov.uk/how_to_find_a_regulated_immigration_adviser

እንዲሁም የሚከተሉትን መገናኘት ትችላለህ፡-

Asylum Advice UK 0808 8000 622
www.asylumhelpuk.org

የ Scotland Aid Scotland (ሌጋል ኤድ ስኮትላን) ህግ ድጋፍ በስኮትላን የሚገኝ
የScottish Legal Aid Board administers Legal Aid. በህግ ድጋፍ ላይ ተጨማሪ መረጃ በሚከተለው አድራሻ ሊገኝ ይችላል፡- 0845 122 8686

የህግ አማካሪ ለማግኘት፡

የScottish Legal Aid Board (ስጂቱሽ ለጋል ኤድ ቦርድ)

http://www.slab.org.uk/public/solicitor-finder/#register

http://oisc.homeoffice.gov.uk/how_to_find_a_regulated_immigration_adviser

የScotland ህግ ባለሙያዎች ማህበር: 0131 226 7411 / www.lawscot.org.uk

**ሰሜን አየርላንድ የህግ ድጋፍ አገልግሎት**
**የሰሜን አየርላንድ የህግ አገልግሎት ኮሚሽን በሰሜን አየርላንድ ውስጥ የህግ ድጋፍ ያስተዳድራል።**

**የህግ ተወካይ ለማግኘት፡-**

http://www.nilsc.org.uk/solicitors.asp?on=solicitors

http://www.lawsoc-ni.org/solicitors-directory/how-to-use-the-solicitors-directory

http://oisc.homeoffice.gov.uk/how_to_find_a_regulated_immigration_adviser

**የምትኖሩበት ቦታ እንግሊዝ ሃገር ወይም ደግሞ ዌልስ ወይ ኖርዘርን አይላንድ ወይም ደግሞ ስኮትላንድ ከሆነ ከ** 0808 8000 622

## 2.15 ስለ ያልተገቡ የህግ ማማከር አገልግሎቶች የሚቀርቡ ግዴታዎች፡-

**ያልተገባ የህግ ምክር ማግኘትህን ከአመንክ ቅሬታህን የማቅረብ መብት አለህ።**

**ጉዳይህንን ለሚመለከተው ድርጅት ቅሬታህን በጽሁፍ ማቅረብ አለብህ።**

**የሚከተሉትን ማካተት ያስፈልጋል፡**

- **ስምና ሙሉ የአድራሻ ዝርዝር፣**
- **የቅሬታ ሙሉ ዝርዝሮች (ጊዜያት ቀናት እና ቦታዎች)፣**
- **የማናቸውም ምስክሮች ዝርዝር (ተገቢ ከሆነ)፣**
- **የደብዳቤዎች ወይም ተገቢነት ያላቸውን ወረቀቶች ቅጂዎች፣**
- **የጉዳይ ማጣቀሻ ቁጥር**

**በመጀመሪያ የህግ አማካሪውን ስታገኘው የደንበኛ እንክብካቤ ደብዳቤ ሊሰጥህ ይገባል። ይህ ደብዳቤ የሚሰሩት ስራ በቅሬታ ማቅረቢያ ስነ-ስርአቶች መሰረት እንደሆነ ያረጋግጣል። ይህም ቅሬታውን ለመመርመር ምን ያህል ጊዜ እንደሚወስድ ያረጋግጣል።**

## 2.16 ለሁኔታዎች ለውጥ

**በሁኔታዎችህ ላይ የተከሰቱ ማናቸውንም ለውጦች ለ** Home office **የማስታወቅ ግዴታ አለብህ ይህም** Asylum Help **(አሳይለም ሄል) ይረዳችዋ ለእርስዎ እና በእርስዎ ተጠግቶ ለሚኖር ሕጻን ልጅም ነው።**

የሚያካተው

- የስም ለውጥ
- ከዚህ በፊት ያልጠቀስከውን ገንዘብ መቀበል ወይም ማግኘት
- የሆነ ነገር ከሸጥክ በኋላ ገንዘብ መቀበል ወይም ማግኘት
- ወደ ተለየ አድራሻ መንቀሳቀስ
- ከትዳር ጓደኛህ ጋር ጋብቻ ፍቺ መፈጸምወይም መለያየት
- ህጋዊ አብሮ የመኖር ስምምነት መመስርት ወይም ከትዳር አጋርዎ ጋር ለመኖር መወሰን
- የሆስፒታል ህክምና ማግኘት
- ስራ መልቀቅ ወይም ደግሞ ስራ መልቀቅ
- እርስዎ (ወይም አጋርዎ) ነፍሰጡር መሆን ወይም ልጅ መውለድ
- ማናቸውም ህፃናት ልጆችዎ ከት/ቤት ወይም ከቤት መውጣት
- ማናቸውም የቤተሰብ አባላቶችዎ ዩናይትድ ኪንግደም (UK) ከእርስዎ ጋር መቀላቀላቸው ወይም ለቀው መውጣት
- ማንኛውም ሰው በአንተ መኖሪያ ውስጥ መቀላቀል ወይም ለቆ መውጣት
- ለእስር ቤት ከገቡ
- ስራ መጀመር Asylum Help ወይም መልቀቅ
- እርጉዝ መሆን እና  የምግብ መግዣ ገንዘብ እና መኖሪያ ቤት የሚሰጥ የነብረው እርዳታ ወደ የምግብ እርዳታ ብቻ ከተቀየረ እና ወይም ደግሞ የቤት እርዳታ ብቻ ከተቀየረ።

በእነዚህ ማናቸውም ሁኔታዎች ላይ የተከሰቱ ለውጦ በድጋፍ መብትህ ላይ ትጽእኖ ሊኖራቸው ስለሚችል Home office ማስታወቅህ ጠቃሚ ነው።

Asylum Help (አሳይለም ሄልፕ) ሊረዳችሁ Home office የእርዳታ ክፍል  ስለማናቸውም ለውጦች በሚከተለው አድራሻህ ማስታወቅ አለባችሁ፡-

Asylum Support Application UK 0808 8000 623
www.asylumhelpuk.org

በተጨማሪም በጣም አስፈልጊ ነው ለየሕግ አማካሪያችሁ እና ኢሚግረሽን ከ Home office(ኢሚግረሽን) ጋር የተያያዘ ክፍል ሁኔታውቹ እንደተቀየረ ማሳወቅ አለባችሁ።

## 2.17 የጤና እንክብካቤ

ጥያቄ ወይም ይግባኝህ በመታየት ላይ እያለ የብሔራዊ ጤና አገልግሎት (NHS) እንክብካቤ ያለ ምንም ክፍያ የማግኘት መብት የለህም። በመጀመሪያ የመኖሪያ አቅርቦት ውስጥ ከሆንክ፣ ወደ መኖሪያህ ለመድረስ ወደ ጤና ምርመራ ልትላክ ትችላለህ።

በመጀመሪያ ደረጃ መኖሪያህ ውስጥ ካልሆንክ ወይም ወደ ተለየ ቦታ ከተላክ፣ አጠቃላይ ሀኪም ተብሎ ወደሚታወቀው ሀኪም በፍጥነት በመመዝገብ አስፈላጊውን የህክምና እንክብካቤ ለማግኘት ትችላለህ። ምዝገባውን ለማካሄድ ስምህን የትውልድ ቀን፣ አድራሻ እና የስልክ ቁ. ማስመዝገብ ያስፈልግሀል። አዲስ የታካሚ ምዝገባ ማረጋገጫ እንዲሁም ያስፈልግሀል። ምናልባትም እዚ ዝትመዘገቡ የ ARC card (ኤ.ር.ክ. ካርድ) ልታሳዩ ልትጠየቁ ትችላላችሁ፡ ይግ ደግሞ ጥገኝነት የጠየቃችሁ መሆናችሁን ለማረጋገጥ እና ያለ ክፍያ እና ገንዘብ የማይከፈልበት የጤና ትበቃ አገልግሎት አንደሚፈቀድማቸው ለማረጋገት ነው።

በ የሕግ ክፍል 95 የ ኢሚግረሽን እና የጥገኝነት ጠያቂዎች ሕግ መሰረት የምትደገፍ ከሆነ ኤችሲ2 (HC2) certificate (ሰርቲፊኬት) ቅጽ ተብሎ የሚታወቀውን የጤና ምስክር ወረቀት ታገኛለህ። ይህም በመጀመሪያ መኖሪያ ወይም ወደ ረዥም ጊዜ መኖሪያ ከደረስክ 18 ቀናት በኋላ ሊሰጥህ ይችላል። ድጋፍን የማታገኝ ከሆነ፣ የኤችሲ1 ቅጽን ማግኘት ያስፈልጋል። ይህ (HC2) የሚባል ሰርቲፊኬት የሚያገልገለው ጊዜ በብዛት ለ ስድስት ወር ነው። ይህ (HC2) ለማሳደስ እንደገና አዲስ ፎርም (HC1) የሚባል ሞሞላት አለበት። ይህ ፎርም በሚቀጥሉት የኢንተርነት አድራሻዎች ማግኘት ይቻላል።

www.nhsbsa.nhs.uk/HealthCosts/1128.aspx.

በተጨማሪም ፎርሙ ከ Job Centre (ጆብ ሰንተር)፡ የጥርስ ሕክምና ቦታ፡ የዓይን ሕክምና ቦታ እና ከፋርማሲ ልታገኙት ትችላላችሁ።

ከስራ እና ጡረታ ሚኒስቴር ዝርዝሮቹን ለማግኘት ትችላለህ።

የኤችሲቲ (HC2) ቅጽ የሚከተሉትን ያስገኙልሀል

- የኤንኤችኤስ ምዝገባዎች (በስኮትላንድ እና ዌልስ ነፃ ነዋሪዎች)
- የኤንኤችኤስ ጥርስ ህክምና እና እንክብካቤ (ማስዋቢያ ነክ ያልሆኑ)
- የእይታ ምርመራዎች
- መነፅሮች እና የእይታ ሌንሶች (ከአይን እይታ ሀኪም የምታመለክትበትን ከፍተኛ ዋጋ ያረጋግጣሉ)
- የኤንኤችኤስ (NHS) ዊጎች እና የጨርቃጨርቅ ድጋፎች/ለምሳሌ የአከርካሪ ወይም የሆድ እቃ ድጋፎች ወይም የቀዶ ጥገና ህክምናዎች በሆስፒታል አማካኝነት የሚቀርቡ (በስኮትላንድ እና ዌልስ ለሚገኙ ነዋሪዎች በነፃ)።

የሳንባ ነቀርሳ ወይም ማንኛውም ሌላ ተላላፊ በሽታ ካለብህ የህክምና ድጋፍ ወዲያውኑ መሻት አለብህ።

በ ለመጀመሪያ ጊዜ የሚሰጣችሁ መኖሪያ ቤት የምትኖሩ Scotland (ስኮትላንድ) ከተማ ከሆነ ይህ የመጀመሪያ መኖሪያ ቤታችሁ ከመቀየራችሁ በፊት አዲስ የሕክምና ቦታ የተመዘገባችሁበት አድራሻ እና የዶቶራችሁ ስም ይሰጣችኋል። በ Scotland (ስኮትላንድ) አዲስ ሰዎች ጥገኝነት የአየቁ ታካሚዎች የ NHS (ኤን.ሄች.ኤስ) አገልግሎት ይሰጣባችኋል ብቻ እንግሊዝ አገር

የሚኖሩ ይሁኒ እንጂ፡ ጥገኝነት የጠየቁት ጉዳያቸው ይሳካላቸው አይ አይሳካላቸው ምን ለውጥ አያሳይም።

## 2.18 ሕፃን ልጅ ከወለዱ በኃላ የሚሰጥ እርዳታ

አንድ ጊዜ ብቻ የሚሰጥ የ £300 አዲስ ልጅ ለወለዱ እናቶች ስደተኞች ጥገኝነት ለጠየቁ የሚሰጥ እርዳታ ነው። ይህ የሚሰጥ እርዳታ ሕጻን ልጅ ሲወለድ ለሕጻኑ የሚይሳስፈልጉት ነገሮች ለመግዛት የሚረዳ እርዳታ ነው። ይህ እርዳታ ለመሰጠት እንዲያስችላችሁ የሚሞላ ፎርም ሕጻን ልጁ ሊወለድ ስምንት ሳምንት ሲቀርበው ወይም ደግሞ ሕጻን ልጁ ተወልዶ 6 ሳምንት እስከሚደርሰው ድረስ መቅረብ ያለበት ፎርም ነው። ከፎርም ጋር አያይዘው ሕጻን ልጁ የሚወለድበት ቀን ያሚያሳይ ከሕክምና ቦታ የሚሰት ማረጋገጫ ወረቀት (MATB1 form) ወይም ደግሞ ሕጻኑ ልጁ የተወለደበት ማረጋገጫ ወረቀት ካልቶም ይህ ማቅረብ ይችላሉ። ለአንድ ልጅ ሲወለድ የሚሰጠው ገንዘብ £300 ሁለት ሲሆኑ (መንታ) ሲሆን የሚሰጠው ገንዘብ £600 ይሰጣችዋል። የሚያገኙት እርዳታ Section 4 (ክፍል 4) መሰረት ከሆነ የሚሰጣችሁ የእርዳታ መጠን £250) ነው። ይህ እርዳታ ለማግኘት ሕጻን ልጁ ከመወለዱ በፊት ከ ስምን ሳምንት በፊት ወይም ደግሞ 6 ሳምንት ሕጻን ልጁ ከተወለደ በኃዋላ ያለው ጊዜ ውስጥ ማመልከቻ መድረስ አለበት።

ሴቶች  እርጉዝ የሆኑ ወይም ደግሞ ሕጻን ልጆች ከ ሶስት ዓመት በታች ያላቸው ከሆኑ እና ጥገኝነት ጠይቀው እርዳታ እየወሰዱ ከሆነ ተጨማሪ እርዳታ £5.00 ለሳምንት ሕጻን ልጆች ዕድሚያቸው ከ አንድ በታች ከሆነ እኛ ሕጻናት ልጆድ ዕድሚያቸው ከ አንድ እስከ ሶስት ከሆነደግሞ £3.00 በሳምንት ከሚሰጣቸው የምግብ መግዣ ገንዘብ ለጥገኝነት ለጠየቁ በላይ።

## 2.19 የቤት ውስጥ በደል

ነይህ ሲባል ለማንኛው ሰው የማስፈራራት እና የማጥቃት ሁኔታ ሲደርስ፡ ከአዋኪዎች መሀክል ወይም ደግሞ ለሕጻናት ልጆች የመምታት ወይድ ደግሞ መጥፎ ስድብ የመስደብ ጠባያት ማሳየት የሚምለከት ሲሆን፡ ባል እና ሚስት በቤትሰብ ውስጥ ወይም ደግሞ ሁለት አዋቂዎች አብሮው ሲነሩ ቆይቶው አንዱ ለሌላው እንዲህ ዓየንት ጠባይ ሲያሳይ፡ ወይም ደግሞ ለሌላ ሰው አብርዎአቸው ለሚኖር፡ ሴግነታቸው ዕድሚያቸው ዘራቸው ማን ወይም ምን ቢይሆን ምንም ትያቁ ሳይኖር።

የቤታዊ ጥቃት ለማንኛውም ሰው ሊሰርስ የሚችል ጥቃት ነው። ሁለቱም የሴት ልጅ እና የወንድ ልጅ ሊደር የሚችል ችግር ነው። ከማን ጋር ይኖራሉ ምን ዓይነት ግንኙት ከሚያጠቃው ሰው እንዳላቸው ቢታወቅም ይህ ችግር ለማንኛውም ሰው ሊደርስ የሚችል ነው። እንደዚህ ዓይነት ችግር ውስጥ እየኖሩ ካሉ ወይ ይህ ዓይነት ጥቃት ሌላ ሰው ወይም ደግሞ ራሳችሁ ይህ ጥቃት ካላችሁ፡በጣም አሰፈላጊ ነው እርዳት ሊሰጣችሁ የሚችልበት መንገድ እንዳለ። ከአቤታዊ ጥቃት እንዳይደርስባችሁ ሁላችሁ መብት አላችሁ፡ ስለ የሚግረሽን ሁኔታችሁ ልዩ ቢሆንም በሳልም እንድትኖሩ መብት አላችሁ።

ይህ ዓይነት ጥቃት ከደረሳችሁ ለ24 ሰዓት ክፍት የሆነ National Domestic Abuse g(ናሽናል ዶመስቲክ አብዩዝ) የሚባል ድርት ጋር ተገናኝትችሁ እርዳታ መተየቅ ትችላላችሁ። እርዳታ ለሚሰቱት የልስክ ቁትር መስመር ስልክ ስትደውሉ ገንዘብ አይከፈልበት 24/7 ስልኩ ክፍት

አው), ፖሊስ፡ የራስዎ ድክቶር፡ የጤና ጥብቃ አገልግሎት፡ የስደተኞች እርዳታ ሰጪ ድርጅቶች፡ በአከባቢያችሁ የሚገኙ እርዳታ ሰጪ ክፍሎች ሊረድዋችሁ ይችላሉ።

ከፈለጉ ከሴት ሰራተኛ መስራት ነው የምፈልገው ማለት ይችላሉ፡ በተጨማሪም ሴት አስተርጋዋሚ እንዲደረግላችሁ መጠየቅ ይችላሉ። እርስዎ የሚሰጡት ዝርዝር በጥብቅ ነው የሚያዘው።

## 2.20 የፍላጎትዎ ወደ አገርዎ መመልስ

ከማጣሪያ ሂደት በኋላ በሁኔታዎች ውስጥ በተከሰተ ለውጥ ወደ ቤትህ ለመመስ ከሻትክ፣ እና የጥገኝነት ማመልከቻህን ለመቀጠል ካልፈለግህ፣ የሚከተሉትን መገናኘት ትችላልህ። Assisted Voluntary Return programme (ኣሲስትድ ቮሉንታርይ ሪተርን ፕሮግራም) የሚባል የመንግስ ቤት ጽሕፈት ክፍል ጋር ተገናኝታችሁ ይህ ዝግጅት ማድረግ ትችላላችሁ። ይ ፕሮግራም በ Home Office(ሆም ኦፊስ) ስር የሚሰራ ፕሮግራም ነው። ተጨማሪ መረጃ ስለዚህ ጉዳይ ካስፈላጋችሁ በሚቀጥሉት የዌብ ሳይት አድራሻ ገብታቹ ማየት ትችላላችሁ።

www.gov.uk/return-home-voluntarily
Voluntary Departures Team; 0300 004 0202

ምርጫዎቹ ወደ አገር ኤት መመል ከሆነ እና ጥገኝነት የጠየቁት ካልፈለጉ፡ እና እዚ አገር መኖር ምንም መብት አሌሎት ከሆኑ፡ እና አገር ቤት መመለስ ከፈለጉ ምናልባት ከ Assisted Voluntrary Return programme (ኣሲስትድ ቮሉንታሪ ረቱርን ፕሮግራም) ተጨማሪ እርዳታ ካስፈሎጎት ወደ የሚቀጥለው የዌብ ሳይት ኣድራሻ ገብታችሁ ተመልከቱ።

www.gov.uk/return-home-voluntarily
Voluntary Departures Team; 0300 004 0202

## 2.21 ቀጥሎ ምን ይከሰታል

ከማጣሪያ ጥያቄ በኋላ ዋና ቃለ-መጠይቅ ይዘጋጃል። በዚህ ደረጃ ላይ የትርጉም እና ማናቸውንም ማስረጃዎች ለማቅረብ የሚረዳዎ የህግ አማካሪ ማግኘቱ ጠቃሚ ነው። የዋና ቃለ-መጠይቅ አጭር ማብራሪያን እባክዎን ይመልከቱ።

ስለ ማመልከቻዎ ድጋፍ ለማግኘት የሚቀርብ ቅሬታ

ማንኛውም የስደተኛ ድጋፍ አገልግሎቶች ለማግኘት ሚሻ ሰው ቅሬታውን ለማቅረብ ይችላል።

በማናቸውም አገልግሎቶቻችን ችግሮች ካጋጠምዎ በመቀጠል ይህንን እንዲያደርጉ እንመክራለን፡

ችግሩን በተቻለዎት ፍጥነት ለስራ ባለድረባ ወይም በጎ ፈቃደኛ አባላችን ማንሳት። ይህ ቅሬታ በአጥጋቢ መልኩ ካልተወገደ በመቀጠል ቅሬታውን በጽሁፍ ለማቅረብ ይችላሉ። ይህንንም ወደ

Asylum Advice UK on 0808 8000 622 በመደወል ወይም ቅጹን ከ

www.asylumhelpuk.org ማውረድ ይችላሉ

ቅሬታ ለማቅረብ ስለፈለጉበት ጉዳይ ለስራ አስኪያጁ መድረስ ያስፈልግዎታል። ቅሬታዎች የግድ በእንግሊዝኛ ቋንቋ መሆን አያስፈልጋቸውም። ይህም በእርስዎ ቋንቋ የሚሆን እና የጥገኝነት ድጋፍ የሚያስተረጉመው ይሆናል። ስራ አስኪያጁ ቅሬታውን የሚመረምር እና ምላሽ የሚያቀርብ ይሆናል። አጥጋቢ ምላሽ ወዲያውኑ ሊሰጥዎት ካልቻለ፣ ማናቸውንም የማስተካከያ እርምጃዎች ዝርዝሮች ለማካተት በ10 የስራ ቀናት ውስጥ እናቀርባለን።

በዚህ የቅሬታ አወጋድ ውጤት ካልረኩ፣ ጉዳዩን የኦፕሬሽኖች ስደተኛ ድጋፍ ዳይሬክተር (በተጠባባቂ ሀላፊነት ወደ ሚያገለግለው) Complaints Officer, Migrant Help, Charlton House, Dover, CT16 1AT ሊያቀርቡ ይችላሉ። አሁንም በዚህ ምላሽ ካልረኩ፣ ቅሬታውን ለማስወገድ እንዳልተቻለ ሊመዘገብ እና ቅሬታውን ሪፖርት ሊያደርጉላቸው ወደሚችሉ ሌሎች ድርጅቶች እንመራዎታለን።

**የዚህን ክፍል ማንኛውም ንዑስ ክፍል አስመልክቶ ማንኛውም ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት እባክዎን የሚከተለው ክፍልን ያነጋግሩ።**

www.asylumhelpuk.org

Asylum Advice UK የጥገኝነት ድጋፍ መስመር (ምክር) 0808 8000 622

Asylum Support Application UK የጥገኝነት ድጋፍ መስመር (የድጋፍ ማመልከቻዎች) 0808 8000 623